ሐሙስ፣ ፌብሩዋሪ 5 ቀን 2026

(10.30 ኤ.ኤም)

SIR ROSS CRANSTON(ሰር ሮስ ክራንስተን)፦ እሺ፣ እዚህ ለተገኛችሁትም ሆነ በቀጥታ ስርጭትለምትከታተሉን ሁሉ እንደምን አደራችሁ። እኔ Ross Cranston ነኝ። ይህ የCranston Inquiry (ክራንስተን ኢንኳይሪ) የመዝጊያ ችሎት ነው። የእኔ ሪፖርት ዛሬ ማለዳ ለፓርላማ የቀረበ ሲሆን፣ አሁን በድረ-ገጻችን ላይ ይገኛል። የዚህ ችሎት ዋና ዓላማ የሪፖርቱን ማጠቃለያዎች እና በሪፖርቱ ውስጥ ያቀረብኳቸውን ምክረ ሃሳቦች በዝርዝር ማቅረብ ነው። ይህንንበይፋ የማከናውነው፣ ሌሎች የምርመራ ችሎቶች በይፋ የተከናወኑበትን ምክንያትመሠረት በማድረግ ሲሆን፣ የምርመራው የአሠራር መመሪያ ዋና አካል የሆኑት የሕዝብን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲታዩ ለማድረግ ነው። በተመሳሳይ ምክንያትም፣ ይህ ችሎት ልክ እንደ ሁሉም የምርመራ ችሎቶች ሁሉ፣ በቀጥታ ስርጭት የሚተላለፍ ሲሆን፣ አላማውም የምርመራው የሥራ ሂደቶችን መከታተል ለሚፈልጉ ሰዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን ማስቻል ነው።

የዚህ ሥራ ትኩረት፣ በርግጥም፣ በኖቬምበር 23 እና 24 ቀን 2021 ዓ.ም የተከሰተው አሳዛኝ ክስተት ሲሆን፣ ከ30 በላይ የሚሆኑ ሰዎች በአነስተኛ ጀልባ ከፈረንሳይ ተነስተው የእንግሊዝ ካናልን (English Channel ለማቋረጥ ባደረጉት ሙከራ ሕይወታቸውን ያጡበትን ሁኔታ ይዳስሳል። ይህ አደጋ፣ በ2018 ዓ.ም የአነስተኛ ጀልባዎች ችግር ለመጀመሪያ ጊዜ ከታወቀበት ጊዜ አንስቶ፣

በአንድ አነስተኛ ጀልባ ላይ ከደረሰ አደጋዎች ሁሉ እጅግ ከፍተኛው ሕይወት የጠፋበት ክስተት ነው። የምርመራው የአሠራር መመሪያ እነዚህን ክስተቶች እንዳጣራ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ይህም መጀመሪያ፣ ሕይወታቸው ያለፈው ሰዎች እነማን እንደሆኑ ለማረጋገጥ፣ በሁለተኛ ደረጃ፣ መቼ፣ የት እና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሞቱ ለመለየት፣ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ከነዚህ ክስተቶች ምን ትምህርት ሊቀሰም እንደሚችል ለመመርመር እና አግባብ ሆኖ ሲገኝም፣ ተመሳሳይ አደጋ የመከሰት ዕድሉን ለመቀነስ ምክረ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው።

የሪፖርቱን ማጠቃለያዎች እና በምርመራው ማብቂያ ላይ ያቀረብኳቸውን ምክረ ሃሳቦች ከመግለጼ በፊት፣ እኔና ባልደረቦቼ፣ በጃንዋሪ 2024 ከተሾምኩበት ጊዜ አንስቶ ሥራችንን እንዴት ስናከናውን እንደቆየንና ያለፍንበትን ሂደት የሚዳስሱ ጥቂት ማብራሪያዎችን መስጠት እፈልጋለሁ። በመጀመሪያ ደረጃ፣ የምርመራው አድማስ በአሠራር መመሪያው መሰረት የተወሰነና የተገደበ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ። እነዚህ መመሪያዎች በዋናነት የሚያተኩሩት በኖቬምበር 23 እና 24 ቀን 2021 በተከሰቱት ክስተቶች ላይ ነው። የምርመራ ቡድኑ ባሕር ለማቋረጥ በአነስተኛ ጀልባዎች የሚደረጉ ጉዞዎችን በአጠቃላይ የመመርመር ሰፊ ሥልጣን የሌለው ሲሆን፣ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘም በፖለቲካዊ፣ ሰብአዊ እና ሕጋዊ ክርክሮች ውስጥ ጣልቃ የመግባት ኃላፊነት የለበትም። በርግጥም፣ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ እና አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

የቀጣዩ ነጥብ፣ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ በድጋሚ ላሰምርበት የምፈልገው ሲሆን፣

ይህ የምርመራ ሂደት ከመንግሥትም ሆነ በሥራችን ወቅት ከመረመርናቸው ልዩ ልዩ የሕዝብ ተቋማት ሙሉ በሙሉ ነፃ እና ገለልተኛ ነው። በሦስተኛ ደረጃ፣ ይህ በሕግ ያልተደነገገ ምርመራ ነው። በመሆኑም፣ ስለ ምርመራው አመራርም ሆነ ስለ ሂደቶቹና የአሠራር ደንቦቹ የሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች በሰብሳቢነቴ በእኔ የሚወሰኑ ሲሆን፣ ይህም ተፈጻሚነት ያላቸውን የሕግ መርሆዎችና በተለይም ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የመሥራት ግዴታን ባገናዘበ መልኩ የሚከናወን መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ። ያለውን ሁኔታ መሠረት በማድረግ፣ በውሳኔዎቼ ውስጥ ሁልጊዜም ትኩረት የምሰጠው ዋና ጥያቄ፡ “ምርመራውን በተሻለ እና ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊያግዝ የሚችለው እና በአሠራር መመሪያው የተጣለብኝን ኃላፊነት እንድወጣ የሚያስችለኝ የትኛው መንገድ ነው?” ለሚለው ጥያቄ ምላሽ መስጠት ነው።

ይህም በቀጥታ ወደ ቀጣዩ ዋና ነጥብ ያመራኛል። የ ምርመራው የአሠራር ሂደቶች በምርመራ ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፣ ከተለያዩ ወገኖች ጋር ውይይት ተደርጎባቸው የተወሰኑ አለመሆናቸውን መግለጽ እፈልጋለሁ። በዚህ ምርመራ ውስጥ ተከራካሪ ወገኖች የሌሉ በመሆኑ፣ ራሱን አቋም ለማስረዳት የሚሞክር ወይም የቀረበበትን ክስ የመከላከል ኃላፊነት ያለበት ማንም ሰው የለም። ከዚህም በተጨማሪ፣ የፍትሐ ብሔር ሆነ የወንጀል ተጠያቂነትን የመወሰን ሥልጣን የሌለኝ መሆኑን መግለጽ እፈልጋለሁ። ከዚህ ይልቅ፣ የምርመራው ዋና ዓላማ እውነታውን በግልጽ ማወቅና ማሳወቅ ነው። በምርመራችን ወቅት

ከእኛ ጋር ግንኙነት የነበራቸው አካላት ሁሉ ሚናቸው እውነታውን ለማረጋገጥ መርዳት ሲሆን፣ ይህም በኖቬምበር 23 እና 24፣ 2021 ሌሊት የነበረውን ሁኔታ በግልጽ ለማወቅ ነው።

ለዚያ መሠረታዊ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽና ድምዳሜ ለመስጠት፣ እኔና ባልደረቦቼ እጅግ ሰፊ እና ጥልቀት ያለው ምርመራ ስናካሂድ ቆይተናል። ለምሳሌ ያህል፣ ለሥራችን አስፈላጊ የሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ገጾችን የያዙ መረጃዎችን ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ለማግኘት የቻልን ሲሆን፤ ይህም ምርመራችን ተሟልቶ እንዲከናወን ትልቅ እገዛ አድርጓል። በመቀጠልም፣ በምርመራው ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላላቸውና ሙሉ ተሳታፊዎች (Full Participants) ብለን ለምንጠራቸው ወገኖች፣ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች አጋርተናል። የደረሰንን መረጃ በዝርዝር የገመገምን በመሆኑ፣ በምርመራው ውስጥ ካሉ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ካላቸው ግለሰቦችና ተቋማት ከ70 በላይ የምስክርነት ቃላትን ማግኘት ችለናል። በተጨማሪም፣ ከምርመራው ጋር ተያያዥነት ባላቸው ልዩ ልዩ ዘርፎች ላይ ሪፖርቶችን እንዲያዘጋጁ ባለሙያዎችን ያሳተፍን ሲሆን፣ እነዚህንም የምስክርነት ቃላትና የባለሙያ ሪፖርቶችን ለሙሉ ተሳታፊዎች አጋርተናል። ከጊዜ በኋላም፣ እነዚህ መረጃዎች በድረ-ገጻችን ላይ የተጫኑ በመሆናቸው፣ ማንኛውም ሰው የችሎቶቹን ሙሉ ቃለ-ጉባኤዎች (transcripts) እና ቪዲዮዎች በዚያው ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይችላል።

በባልደረቦቼ የብዙ ወራት ጠንካራ የሥራ ውጤት፣ እንዲሁም በሙሉ ተሳታፊዎች እና እንደ አር.ኤን.ኤል.አይ (RNLI) ባሉ ወገኖች መልካም ትብብር ምክንያት፣ ባለፈው ዓመት በማርች መጀመሪያ ላይ ሙሉ ችሎቶቻችንን ለመጀመር እና በአራት ሳምንታት ውስጥ ለማጠናቀቅ ችለናል።

በዚያው ወቅት፣ በምርመራው የሕግ አማካሪዎች አማካኝነት እኔ ስም ጥያቄ የቀረበላቸውን የ22 ምስክሮች የቀጥታ የምስክርነት ቃል ሰምቻለሁ። በተጨማሪም፣ በምርመራ ቡድኑ የሕግ አማካሪ የቀረቡ የመክፈቻ መግለጫዎችን፣ እንዲሁም በሙሉ ተሳታፊዎች ተወካይ የሕግ አማካሪዎች የቀረቡ የመክፈቻና የመዝጊያ መግለጫዎችን ሰምቻለሁ።

በሙሉ ችሎቶቹ የመጨረሻ ሳምንታት ውስጥ፣ የሟቾችን ቤተሰቦች የጉዳት መግለጫ መስማት ችያለሁ። መግለጫዎቹ በቤተሰቦቹ የትውልድ ቋንቋ የተመዘገብ በመሆናቸው፣ እነዚሁ በምስልና በድምፅ የተመዘገቡ መረጃዎች በችሎቱ አዳራሽ ውስጥ እንዲቀርቡ ተደርጓል።  ከምርመራ ቡድኑ አባላት መካከል አንዱ፣ እያንዳንዱ የድምፅና ምስል ማስረጃው ቀርቦ እንደተጠናቀቀ፣ መግለጫውን በእንግሊዝኛ ቋንቋ መልሶ ያነብ ነበር።  እነዚያ የቤተሰብ አባላት ለሰጡት ምስክርነት በድጋሚ ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ።  የሪፖርቴ አንዱ ክፍል በካናሉ አሰቃቂ አደጋ ሕይወታቸውን ላጡ ወገኖች መታሰቢያነት ልዩ ትኩረት የሰጠ ሲሆን፣ አደጋው በሰዎች ሕይወት ላይ ያሳደረውንም ተፅዕኖ በዝርዝር ይዳስሳል።

ይህም የምርመራ ሂደቱ በቋሚነት የሚከተለው ወጥ መገለጫ ነው።  የሟቾችን ቤተሰቦች የሥራችን ዋነኛ ትኩረት ለማድረግ የጣርን ሲሆን ሁሌም ማስታወስ ያለብን ከኖቬምበር 23 እስከ 24 ቀን 2021 ዓ.ም ሕይወታቸውን ላጡ ወገኖች፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለወዳጆቻቸው ይህ ክስተት ከምንም በላይ እጅግ ዘግናኝ የሆነ ሰብአዊ አደጋ  መሆኑን ነው።

ወደ ሪፖርቱ ዋና ሐሳብ ከመመለሴ በፊት፣ ሁለት ሌሎች አስፈላጊ

ጉዳዮችን መጥቀስ ይኖርብኛል። የመጀመሪያው ጉዳይ ከMarine Accident Investigation Branch (MAIB፣ ባሕር ላይ አደጋ ምርመራ ቅርንጫፍ) ጋር የተያያዘ ነው። ከክስተቱ በኋላ፣ MAIB ስለ ጉዳዩ የደኅንነት ምርመራ ማካሄድ ጀምሮ ነበር። ሪፖርታቸው የታተመው በኖቬምበር 8 ቀን 2023 ዓ.ም ሲሆን፣ ይህም የእኔ ሹመት ይፋ ከመደረጉና ምርመራው ከመጀመሩ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ነበር። የእኔ ምርመራ ከMAIB የተለየ የሥራ ኃላፊነት (remit) ነበረው። እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ ስለ ሟቾች የሚነሱ ጥያቄዎችን መመለስ የMAIB የሥራ ድርሻ አካል አልነበረም። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፣ ይህ ለምርመራው ሂደት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አይተናል።

ይሁን እንጂ፣ የእኔ የሥራ መመሪያ በዋናነት የMAIBን ምርመራ ግምት ውስጥ እንዳስገባ ያዛል። እኔና ባልደረቦቼ ይህንን ተግባር በከፍተኛ ጥንቃቄ ያከናወንን ሲሆን፣ በምርመራ ሥራችን ወቅትም ደጋግመን እንደ መረጃ ምንጭ ተጠቅመንበታል። ከዚህም በላይ፣ በዝርዝር እንደምገልጸው፣ በሪፖርቱ ማጠቃለያ ላይ ከቀረቡት ምክረ ሐሳቦች አንዱ፣ ከMAIB ምርመራ በኋላ የወሰዷቸውን የአፈጻጸም እርምጃዎች ለሕዝብ ይፋ የማድረግን አስፈላጊነት የሚመለከት ሲሆን፣ ይህም በተለይ ከምርመራ በኋላ የሚወሰዱ እርምጃዎችን የሚመለከት ይሆናል።

እዚህ ደረጃ ላይ ልመለከተው የሚገባኝ ሁለተኛው ጉዳይ፣ የፈረንሳይ ባለሥልጣናት ያላቸውን አቋም የሚመለከት ይሆናል።

ከኖቬምበር 23 እስከ 24 ቀን 2021 ዓ.ም የተከሰቱትን ድርጊቶች ተከትሎ፣ የፈረንሳይ ባለሥልጣናት ከክስተቱ ጋር በተያያዘ የወንጀል ምርመራ የጀመሩ ሲሆን፣ የምርመራ ሂደቱም በመርማሪ ዳኛ አማካኝነት እየተመራ ይገኛል። ምርመራው ቡድኑ የፓሪስ አቃቤ ሕግን በፈረንሳይ ምርመራ የተያዙ ማስረጃዎችን እንዲያጋራ የጠየቀ ቢሆንም፣ በሕጋዊ የምስጢር አጠባበቅ ደንብ መሠረት፣ ይህ ሊሆን እንደማይችል ምላሽ ተሰጥቶታል። የፈረንሳይ የወንጀል ሕግ በእንደዚህ ዓይነት ምርመራዎች ውስጥ በሚሳተፉ አካላት ላይ የምስጢር የመጠበቅ ግዴታን ይጥላል። የዚህም ውጤት፣ የምርመራ ቡድኑ አሁንም በሂደት ላይ ካለው የፈረንሳይ ምርመራ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለማግኘት አለመቻሉ ነው።

ይሁን እንጂ፣ የፓሪስ አቃቤ ሕግ ትብብር በማድረግ፣ በትንሿ ጀልባ ላይ ተሳፍረው ሊሆኑ የሚችሉትን የሟቾች እና የጠፉ ሰዎችን ማንነት የሚገልጽ ዝርዝር ለምርመራ ቡድኑ እንዲደርሰው አድርጓል። በተጨማሪም፣ ምርመራ ቡድኑ ስለ ራሱ የሥራ ሂደት ለፈረንሳይ ባለሥልጣናት መረጃ ሲያቀርብ መቆየቱን ለመግለጽ እወዳለሁ።

አሁን ወደ ሪፖርቱ እመለሳለሁ። በመጀመሪያ፣ ስለ ረቂቅ ሂደቱ አንድ ነገር ማለት እወዳለሁ። ባለፈው ዓመት ማርች ወር ላይ ሙሉ የችሎት ሂደቶች ከተጠናቀቁ በኋላ፣ እኔና የሥራ ባልደረቦቼ ሪፖርቱን በማርቀቅ ተግባር ላይ ተሰማርተናል። በዚያ ጊዜ፣ በሙሉ የችሎት ሂደቶች ላይ ከቀረቡ ነጥቦች በመነሳት፣ ከበርካታ አካላት ተጨማሪ ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥረት አድርገናል። ባለፈው ዓመት ክረምት ወቅት

ገና ያልጸደቀው ሪፖርት ወደ መጠናቀቅ ደረጃ ላይ በደረሰ ጊዜ፣ በምርመራው ሊቀርቡ የታሰቡ ትችቶችን ለሚመለከታቸው ድርጅቶች አሳውቋል። በተጨማሪም፣ ገና ያልጸደቁ ምክረ ሐሳቦችን ለሚመለከታቸው ድርጅቶች በመላክ፣ የውሳኔዎቹን ተግባራዊነትና አፈጻጸም በሚመለከት አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ጋብዘናል። ከሁለቱም ወገኖች የተገኙትን ምላሾች ገምግሜ እንደጨረስኩ፣ ጠቃሚ ሆነው ያገኘኋቸውን ነጥቦች እንዲሁም ለጊዜያዊ ትችቶቹና ምክረ ሐሳቦቹ የተሰጡ ትክክለኛ ምላሾችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ተገቢ በሆኑ ቦታዎች ላይ የመጀመሪያውን ገና ያልጸደቀ ሰነድ ላይ ማሻሻያ አድርጌያለሁ።

ይህንን ሪፖርት ባዘጋጀሁበት ወቅት፣ ግምት ውስጥ ያስገባኋቸው በርካታ መሠረታዊ መርሆች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ፣ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀል ተጠያቂነትን የመወሰን ሥልጣን የሌለኝ መሆኑን እና ምንም ዓይነት የጥፋተኝነት ድምዳሜ ላይ እንዳልደረስኩ ልገልጽ እወዳለሁ። ከዚህ ይልቅ፣ የሥራዬ ዋና ግብ በኖቬምበር 23 እና 24 ቀን 2021 ዓ.ም ምን እንደተከሰተ እውነቱን ማውጣት ሲሆን፣ ከምርመራው እና ከድምዳሜዎቼ በመነሳት፣ አስፈላጊ ናቸው ቤዬ ያመንኩባቸውን ምክረ ሐሳቦች ማቅረብ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ፣ በምርመራው የማጣርያ ሒደት መሠረት፣ ማስረጃ የማቅረብ ኃላፊነት በማንም ላይ ያልወደቀ ሲሆን፣ እውነታዎችን ለማረጋገጥ የምንመራባቸው ቋሚ መመዘኛዎች አልነበሩም። አንድ ድርጊት ስለመፈጸሙ ወይም ስላለመፈጸሙ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ፣ ነገሮችን በማመዛዘን ላይ የተመሰረተ እንደ ሁኔታው የሚለዋወጥ አቀራረብን ተከትያለሁ። በአብዛኛው፣ የቀረበው ማስረጃ ግልጽ በመሆኑ፣ አንድ ክስተት ስለመፈጠሩ ምንም ዓይነት

ክርክር ሊነሳ አይችልም። በሌሎች ሁኔታዎች፣ የእኔ ድምዳሜ አንድ ክስተት ተከስቶ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን፣ በአማራጭ ደግሞ፣ ክስተቱ ተከስቶ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል። አንዳንዴ፣ እርግጠኝነት የጎደላቸው ነገሮች ቢኖሩም፣ እንደ እኔ እይታ፣ በምርመራው ዋና ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አላመጣም።

በመጨረሻም፣ ድምዳሜዬ ላይ፣ በዚያች ሌሊት በነበሩት ክስተቶች ውስጥ ተሳታፊ የነበሩትን ሰዎች ድርጊትን ስመዝን ከክስተቱ በኋላ በሚታወቅ እውቀት ላይ ተመስርቶ መፍረድን ለመከላከል ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጌያለሁ። በዚያች ሌሊት በሰዎች ላይ የታዩ ጉድለቶችን ለይቼ ያወጣሁ ቢሆንም፣ እያንዳንዱን ሁኔታ በወቅቱ ከነበረው ግንዛቤ፣ አቅም፣ ከተደረጉት ቅድመ ዝግጅቶች እና በሥራ ላይ ከነበሩት የአሠራር ሥርዓቶች አንጻር መዝኜዋለሁ።

ባጠቃላይ፣ በግለሰቦች ላይ የሚታዩ ጉድለቶች ለክስተቱ እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ ቢሆኑም፣ ዋናው መንስኤ ግን ከሥርዓታዊ ችግሮች የመነጩ ናቸው። እነዚህን ነጥቦች ካለው ሁኔታ ጋር በማያያዝ በጥልቀት መመርመሩ በሪፖርቱ ለተካተቱት ምክረ ሐሳቦች መሠረታዊ ምንጭ ሆኗል።

ሪፖርቱ ከ450 ገጾች በላይ የሚሸፍን ነው። ስለ ድምዳሜዎቹ እና ምክረ ሃሳቦቹ አጭር ማጠቃለያ ከመስጠቴ በፊት፣ የምርመራ ውጤቶቹን ሙሉ በሙሉ ለመረዳትና ለመገንዘብ፣ ሙሉውን ጽሑፍ ከማንበብ የተሻለ አማራጭ እንደማይኖር አስቀድሜ ለመግለጽ እወዳለሁ። ይሁን እንጂ፣ ለግንዛቤ እንዲረዳ በሪፖርቱ መግቢያ ላይ፣ ባለ 15 ገጽ ዋና ማጠቃለያ ተካቷል።

እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ቁልፍ ነጥብ ቀጥሎ የማቀርበው ከሪፖርቱ የተወሰደ

እጅግ የተጨመቀና በጣም አጭር መግለጫ ሲሆን፣ ይህም በሪፖርቱ ውስጥ ያሉ ዝርዝር መረጃዎችና ማስረጃዎች ያልተካተቱበት ከመሆኑም በላይ፣ ለድምዳሜዎቹ ጥንካሬ የሚሰጡ ዝርዝር ምክንያቶች በዚህ አጭር መግለጫ ውስጥ አልተካተቱም።

ያንን ማሳሰቢያ በመጥቀስ፣ በሥራ መመሪያው ላይ ወደተቀመጠው የመጀመሪያ ጥያቄ ስንሸጋገር፣ በኖቬምበር 23 እና 24 ቀን 2021 ዓ.ም በኢንግሊዝ ካናል ላይ ሕይወታቸውን ያጡት ግለሰቦች እነማን ነበሩ?

ምርመራው ሕይወታቸውን ካጡት 27 ሰዎች መካከል የ26ቱን ማንነት በልበ ሙሉነት ለማረጋገጥ የቻለ ሲሆን፣ በጀልባዋ ላይ እንደነበሩ የሚታመን ቢሆንም እስካሁን አስከሬናቸው ያልተገኘውን የአራት ሰዎችን ማንነት ጭምር ለመለየት ተችሏል። አስከሬኑ የተገኘው የ27ኛው ሰው ማንነት በእርግጠኝነት ሊረጋገጥ ባይችልም፣ ምርመራው ግለሰቡ ማን ሊሆን እንደሚችል ግምቱን አቅርቧል። በተጨማሪም ሪፖርቱ ከአደጋው የተረፉትን ሁለት ሰዎች ማንነትም ያካትታል። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዱ፣ በሙሉ የችሎት ሂደቱ ላይ ቀርቦ ምስክርነቱን ሰጥቷል።

በዚህ መሠረት ቢያንስ 33 ሰዎች -- ወንዶች፣ ሴቶች እና ሕፃናት -- በዚያች በኖቬምበር 23 ቀን 2021 ዓ.ም ምሽት ከፈረንሳይ በተነሳችው አነስተኛ ጀልባ ውስጥ ነበሩ። ምርመራው በጀልባዋ ላይ ሌሎች ተጨማሪ ሰዎች አለመኖራቸውን በእርግጠኝነት ማረጋገጥ ባይችልም ቤተሰቦቻቸው የደረሱበትን መቼም ቢሆን በእርግጠኝነት ሊያውቁ የማይችሉ ሕፃናትን ጨምሮ ሌሎች ተሳፋሪዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገመታል።

አብዛኛው የሪፖርቱ ክፍል -- እንዲያውም ከመጀመሪያው እና ከመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች ውጭ ያለው በሙሉ -- ትኩረት የሚያደርገው በሥራ መመሪያው ላይ

በተቀመጡት ቀሪ ቁልፍ ጥያቄዎች ላይ ሲሆን ይኸውም ሟቾቹ መቼ፣ የት እና በምን ዓይነት ሁኔታዎች ለሞት እንደተዳረጉ ያብራራል? ለእነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡትን መደምደሚያዎች ከመዘርዘሬ በፊት በዚያ ምሽት የተከሰተውን ሁኔታ በጣም አጭር በሆነ ማጠቃለያ ማቅረቡ ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ታሪካችንን የምንጀምረው ህገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች ለባሕር ጉዞ የማይመጥን እና ከአቅም በላይ ሰው የጫነች አነስተኛ ጀልባን በዚያች የኖቬምበር 23 ቀን 2021 ዓ.ም ምሽት በግምት ከምሽቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ከፈረንሳይ የባሕር ዳርቻ ባስነሱበት ወቅት ነበር። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፣ በጀልባዋ ላይ ቢያንስ 33 ሰዎች ተሳፍረው ነበር። ተሳፋሪዎቹ እጅግ በተጨናነቀ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ። እነዚህ ተሳፋሪዎች በጀልባዋ ላይ ቦታ ለማግኘት ለሕገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች በሺዎች የሚቆጠር ፓውንድ የከፈሉ ሲሆን፣ ይህንን ጉዞ የጀመሩት ወደ ዩናይትድ ኪንግደም በሰላም እንደሚሻገሩ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ነበር። ከተሳፋሪዎቹ መካከል ሕይወታቸው ሊተርፍ የቻለው የሁት ሰዎች ብቻ ነበሩ።

ጀልባዋ ለደረሰባት አደጋ መንስኤው ምን እንደሆነ በአሁኑ ወቅት በእርግጠኝነት ለመናገር አንችልም። ሆኖም ግን፣ ጉዞው ከተጀመረ ከሦስት ሰዓታት በኋላ ጀልባዋ በከፍተኛ መጠን ውኃ ማስገባት የጀመረች ሲሆን ትንሽ ቆይቶም ሙሉ በሙሉ በውኃ ተሞልታ መስመጥ ጀምራለች። ተሳፋሪዎቹ የገባውን ውኃ ለማስወጣት ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ በመቅረቱ፣ በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ሆነው እርዳታ ለማግኘት በሞባይል ስልካቸው ተደጋጋሚ ጥሪዎችን ለማድረግ ሞክረዋል። ከተሳፋሪዎቹ አንዱ ጉዞውን ላመቻቸው ሕገወጥ አዘዋዋሪ በመደወል የነበሩበትን ቦታ መረጃ ልኮለት ነበር። ግለሰቡ ለመርዳት ያደረገው ምንም ነገር አልነበረም።

የኖቬምበር 24 ቀን 2021 ከለሊቱ 1 ኤ.ኤም አካባቢ፣ የ ፈረንሳይ የባሕር ዳርቻ ጥበቃ ለHis Majesty's Coastguard (ግርማዊነታቸው የባሕር ዳርቻ ጥበቃ) በሰጠው መረጃ መሠረት፣ 33 ሰዎችን የያዘች አነስተኛ ጀልባ በእንግሊዝ ካናል አካባቢ ግማሽ ኖቲካል ማይል (nautical mile) ርቀት ላይ እንደነበረች ታወቀ።

HM Coastguard ለዚህ አደጋ "Charlie" (ቻርሊ) የሚል የመለያ ስም ሰጥቶታል። ብዙም ሳይቆይ የፈረንሳይ ባለሥልጣናት ከጀልባዋ ላይ በአንድ የ16 ዓመት ወጣት የተደረገን የእርዳታ ጥሪ ለሚመለከተው ክፍል አስተላለፉ። ታዳጊው ለ20 ደቂቃ ያህል ለHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ መረጃ ሲሰጥ ቆይቷል። እሱም “ውኃ ውስጥ ነን” በማለት አስቸኳይ የነፍስ አድን እርዳታ እንዲደረግላቸው ጠይቋል። የጀልባዋ መገኛ ቦታ (Geolocation) መረጃ ለHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ የተላከ ሲሆን፣ ይህም ጀልባዋ ካናል ውስጥ በሚገኘው ሳንዴቲ (Sandettie) ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በመሃከለኛው መስመር አቅራቢያ፣ በዩናይትድ ኪንግደም በኩል እንደነበረች ያሳያል።

አደጋ ላይ ከነበረችው ጀልባ የተላኩ በርካታ ተስፋ አስቆራጭ ጥሪዎችና መልእክቶች ቢኖሩም አንዳንዶቹ ጥሪዎችና መልእክቶች ግን ሳይደመጡ አልፈዋል። HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ የሜይዴይ ሪሌይ (Mayday relay) ስርጭት ያስተላለፈ ቢሆንም፣ በአቅራቢያው የነበረችው Flamant (ፍላማንት) የተሰኘችው የፈረንሳይ የባሕር ኃይል መርከብ ምንም ዓይነት ምላሽ አልሰጠችም። ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ከለሊቱ 1.30 ኤ.ኤም. አካባቢ፣ የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ፣ Valiant (ቫሊያንት) የተሰኘችውን የድንበር ኃይል ጀልባን) አሰማራ። Valiant ከDover ወደብ ተነስታ ለመውጣት እስከ ለሊቱ 2.22 ኤ.ኤም. የዘገየች ሲሆን “Charlie” የተሰኘው ክስተት ለመጨረሻ ጊዜ ታውቆ የነበረበት ቦታ

ለመድረስም ሌላ ተጨማሪ አንድ ሰዓት ፈጅቶባታል። ልክ ከለሊቱ 3 ኤ.ኤም. በፊት Valiant በመጓዝ ላይ እያለች የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ R163 የተሰኘች ሄሊኮፕተርንም ለፍለጋ እና ነፍስ አድን ተልእኮ አሰማራ።

Valiant ከለሊቱ 3.24 ኤ.ኤም. አካባቢ ሳንዴቲ በምትባለው ስፍራ ብትደርስም ጀልባዋን ማግኘት አልቻለችም። ጀልባዋ ያለችበት የመገኛ ነጥቦች (Coordinates) ከአንድ ሰዓት ተኩል በፊት ቀደም ብሎ ለድንበር ኃይል ተሰጥተው የነበረ ቢሆንም፣ Valiant በቦታው በደረሰችበት ወቅት አነስተኛዋ ጀልባ በውኃው ተገፍታ ከነበረችበት ስፍራ ርቃ ሳትሄድ እንዳልቀረች ይገመታል። ከለሊቱ 3.30 - 7.20 ኤ.ኤም. ባለው ጊዜ ውስጥ ሄሊኮፕተሯ እና Valiant ሦስት አነስተኛ ጀልባዎች ያሉበትን ቦታ ለማግኘት ችለዋል። Valiant በድምሩ 98 ሰዎችን ወደ መርከቧ ጭናለች። Valiant ያገኘቻቸው ጀልባዎች በሙሉ "Charlie" ተብሎ ከተገለጸው ክስተት መግለጫ ጋር የሚመሳሰሉ አልነበሩም።

ከጠዋቱ 7 ኤ.ኤም. ገደማ ፀሐይ ወቶ በውኃው ላይ ብርሃን ሲያርፍ፣ አንዳንድ ሰዎች በጀልባዋ ፍርስራሽ ላይ ተንጠልጥለው እንደነበር በሕይወት ከተረፉት ሁለት ሰዎች አንዱ ለምርመራው ተናግሯል። የሌሎች ሰዎች አስከሬን በዙሪያቸው በውኃው ላይ ተንሳፎ ይታይ እንደነበርም ገልጿል። አንዲት እናት ልጆቿን ስትፈልግ ታሰማው የነበረው አሰቃቂ ጩኸት አሁንም ድረስ እንደሚታወሰው ምስክሩ ገልጿል። በዚህ ሰአት፣ ሄሊኮፕተሩ ፍለጋውን እንድያበቃ ተደርጎ የነበረ ሲሆን፣ Valiant ያሳፈረቻቸውን 98 ሰዎች ይዛ ወደ Dover በመመለስ ላይ ነበረች። በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ጀልባዋን የሚፈልጋትም ሆነ ለእርዳታ የደረሰላት ማንም አልነበረም።

በዚያኑ ዕለት ኖቬምበር 24 ቀን 2021 ከቀኑ 12.30 ፒ.ኤም. ገደማ፣ ከCalais (ካሌስ) የባሕር ዳርቻ በግምት 9 ኖቲካል ማይል (nautical miles) ርቆ በመጓዝ ላይ የነበረው አንዲት የፈረንሳይ የዓሣ አጥማጅ መርከብ ውኃው ላይ ተንሳፈው ከነበሩት አስከሬኖች መካከል የመጀመሪያውን አግኝቷል። የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ መረጃው የደረሰው፣ የመጀመሪያውን የነፍስ አድን ጥሪ ካስተናገደ ከ12 ሰዓታት በኋላ በግምት 1 ፒ.ኤም. አካባቢ ነበር። በመጨረሻም፣ በጀልባዋ ላይ የነበሩት ሰዎች አስከሬን ወደ ፈረንሳይ የተወሰደ ሲሆን ሁለት በሕይወት የተረፉ ሰዎች ደግሞ ከአደጋው መዳን ችለዋል።

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፣ ይህ በዚያች ሌሊት የተከሰተውን ሁኔታ የሚያሳይ በጣም አጭር መግለጫ ቢሆንም፣ ማብራሪያው ምርመራው ለምን እንደተካሄደ በተወሰነ መልኩ ያስረዳል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

በሪፖርቱ ክፍል 3 ምዕራፍ 8 ውስጥ እኔና ባልደረቦቼ በምርመራችን ሂደት የታዘብናቸውን በርካታ የሰነድ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን በመጠቀም በዚያች ሌሊት የተከሰቱት ክስተቶች ዝርዝር አቅርበናል።

ለዚያ ዘገባ ተገቢውን ሁኔታዊ መግለጫ ለመስጠት ሲባል ከምዕራፍ 2 እስከ 7 ያሉት የሪፖርቱ ክፍሎች አግባብነት ያለውን የሕግ ማዕቀፍ እንዲሁም ዩናይትድ ኪንግደም በባሕር ላይ ለፍለጋና ነፍስ አድን ተግባር ያለባትን ሕጋዊ ግዴታዎች በዝርዝር አቅርቧል። እነዚህ ምዕራፎች ባሕር ለማቋረጥ በአነስተኛ ጀልባዎች የሚደረጉ ጉዞዎች በ2018 ዓ.ም ጎልተው መታየት ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ያለውን ታሪክ የሚያሳዩ ሲሆን፣ እነዚህ ጉዞዎች ለፍለጋና ነፍስ አድን ሥራ የሚፈጥሩትን ተግዳሮቶችም ለይተው ያሳያሉ።

በተጨማሪም እነዚህ ምዕራፎች ለአነስተኛ ጀልባዎች እንቅስቃሴ ምላሽ በመስጠት ረገድ ተሳታፊ የሆኑትን ቁልፍ የዩናይትድ ኪንግደም እና የፈረንሳይ ድርጅቶችን የሚዘረዝሩ ሲሆን፣ የዩናይትድ ኪንግደም መንግሥት እየጨመረ ለመጣው የጉዞ ቁጥር የሰጠውን ምላሽ እና እስከ ኖቬምበር 2021 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ የተደረጉ አሠራሮችን ይተነትናሉ።

በምዕራፍ 8 ላይ ከቀረበው ዝርዝር ዘገባ በመቀጠል ከምዕራፍ 9 እስከ 12 ያሉት የሪፖርቱ ክፍሎች በዚያች ሌሊት በዩናይትድ ኪንግደም የፍለጋና ነፍስ አድን አገልግሎቶች ተዘጋጅተው የነበሩትን ሀብቶችን ከመገምገሙ በላይ፣ "Charlie" ተብሎ ለተሰየመው ክስተት የተሰጠውን የመጀመሪያ ምላሽ እና ስለ አደጋው ተፈጥሮ የተከናወነውን የመረጃ አሰባሰብ ይመረምራሉ። ቀጣዮቹ ምዕራፎች የተከናወነውን የፍለጋ ተግባር የሚገመግሙ ሲሆን፣ "Charlie" በተሰኘው ክስተት ላይ የነበረችው አነስተኛ ጀልባ ደኅንነቷ ተጠብቆ ተገኝታለች የሚል የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ለመደረሱ መነሻ የሆኑ ክስተቶችን በዝርዝር ይዳስሳሉ።

በዚህ ጥልቅ ምርመራ መሠረት ሙሉ ዝርዝር መረጃዎቹ በራሱ በሪፖርቱ ውስጥ መስፈራቸውን ድጋሚ ላሳስብ እወዳለሁ። የሪፖርቱ ምዕራፍ 15 በዚያች ሌሊትና በማግስቱ ጠዋት ከደረሱት የሞት አደጋዎች መካከል የተወሰኑት መከሰት ያልነበረባቸው እንደነበሩ ያረጋግጣል። ሐሳቡን በአጭሩ ለመግለጽ የተደረገው ጥልቅ ምርመራ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በመጀመሪያም፣ MAIB በሪፖርቱ ላይ የደረሰበትን መደምደሚያ እቀበላለሁ፣ እርሱም፡-

"ለባሕር ጉዞው የማይመጥን ጀልባ እና በቂ ያልሆነ የደኅንነት መሣሪያዎችን በማቅረብ እንዲሁም 33 ሰዎችን በጀልባዋ ላይ በማጨናነቅ የጉዞ ሙከራውን ያመቻቹት ግለሰቦች በጀልባዋ ላይ የነበሩትን ተጓዦች ለከፍተኛ አደጋ እና ለጉዳት ዳርገዋቸዋል።"

ሁለተኛ ደረጃ፣ የሰዎችን ከአደጋ የመትረፍ ዕድል የሚያጠናው የምርመራው ባለሙያ በደረሰበት መደምደሚያ መሠረት፣ ውኃ ውስጥ ሲወድቁ የሚያጋጥመውን በቅዝቃዜ የሚመጣ ድንገተኛ የሰውነት መቆጣት (cold water shock) መቋቋም ቢችሉም እንኳ፣ የአነስተኛ ጀልባዋን ተንሳፋፊ ስብርባሪዎች ጨብጠው መቆየት እስከማይችሉበት ጊዜ ድረስ ቆይተው ሰምጠዋል። ይህም የሆነው፣ በቅዝቃዜው ሳብቢያ የእግር እና የእጅ እንቅስቃሴ በመገታቱ፣ራስን በመሳት ወይም በብርድ ምክንያት ልባቸው ሥራ በማቆሙ ምክንያት ነው።

ስለሆነም የየድንበር ኃይል መርከብ Valiant በኖቬምበር 24 ቀን 2021 በግምት ከሌሊቱ 3.24 ኤ.ኤም. አካባቢ ሜይዴይ ሪሌይ ወደተጠቆመበት ቦታ በደረሰችበት ወቅት አብዛኞቹ ተጓዦች በሕይወት እንደነበሩ ይገመታል። በተጨማሪም በአነስተኛዋ ጀልባ ላይ ከነበሩት ሰዎች አንዳንዶቹ በዚያን ቀን ፀሐይ ስትወጣ በጠዋቱ 7 ኤ.ኤም. ገደማ በሕይወት እንደነበሩ የሚታመን ሲሆን፣ በእዚያ ሰዓት እና በዚያው ዕለት ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ሕይወታቸው ሊያልፍ ችሏል። በዚህም መሰረት በባለሙያው ግኝት እና ከአደጋው ከተረፈው ሰው በተገኘው ማስረጃ መካከል ያለው መረጃ የተጣጣመ መሆኑን አስተውያለሁ ለሙሉ የምርመራ ሂደቱ በሰጠው ቃል መሠረት ሰዎች ውኃ ውስጥ ከወደቁ በኋላም በሕይወት ለመቆየት የቻሉ ሲሆን እስከ ጠዋት ድረስ 10 የሚሆኑ ሰዎች በሕይወት ነበሩ።

በሶስተኛ ደረጃ፣ የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂን በተመለከተ፣ በDover በሚገኘው Maritime Rescue Coordination Centre (የባሕር ላይ ነፍስ አድን አስተባባሪ ማዕከል) የነበረውን የሰው ኃይል ስምሪት እና ክስተቱ ያሳደረውን ተጽዕኖ በጥንቃቄ

መርምሬያለሁ።

## በቂ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ከመመደብ ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች

በHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ውስጥ ተደጋግመው የታዩና አስቀድመው የታወቁ ጉዳዮች ነበሩ። ይህ ሁኔታ ከአደጋዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑ በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን፣ ይህም ጉድለት ባለበት ምላሽ  ሳቢያ የሚከሰት የሕይወት መጥፋትን፣ ወቅታዊ ሁኔታዎችን የመገንዘብ አቅም ማጣትን እንዲሁም በሠራተኞች ደኅንነት እና የሥራ ተነሳሽነት ላይ መጥፎ ተጽዕኖ ይፈጥራል።  እውነታው ግን የሚያሳየው፣ በDover የነበረው የሰው ኃይል በኖቬምበር 23 እና 24 ቀን 2021 ዓ.ም ሌሊት የተፈጠረው ሁኔታ ከአቅሙ በላይ ሆኖበት እንደነበር ነው።  ቀደም ብዬ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት፣ የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ስለነዚህ ችግሮች እና ተዓዳኝ አደጋዎች ግንዛቤ ነበረው።  ምርመራው ከኖቬምበር 2021 ዓ.ም በፊት ጉዳዮቹን እንዴት ለመፍታት አንደተሞከረ የሚያብራራ በቂ ማስረጃ አላገኘም።

በተጨማሪም ከኖቬምበር 2021 ዓ.ም በፊትም ሆነ በኋላ የትራንስፖርት መምርያ በMarine and Coastguard Agency (ባሕር እና የባሕር ዳርቻ ጥበቃ ኤጀንሲ) ላይ የነበረው ቁጥጥር፣ እንዲሁም በMCA በኩል በHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ላይ የሚይያደርገው ክትትል ጉድለት ያለበት እንደነበር አረጋግጫለሁ።  ተገቢ የሆነ የክትትል ሥርዓት ባለመኖሩ፣ ለውጥ የሚሹ ችግሮች የትኞቹ እንደሆኑ፣ በበቂ ሁኔታ ሳይለይ ወይም ትኩረት ሳይሰጠው ቀርቷል።

በዚያች ሌሊት ወደተከናወነው የፍለጋ እና ነፍስ አድን ሥራ ስንመለስ፣ ሁለት ቁልፍ ነጥቦችን ለይቼ አስቀምጫለሁ።  የመጀመሪያ ጉዳይ የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ በኖቬምበር

24 ሌሊት 2.27 ኤ.ኤም. እንዲሰራጭ ያደረገው የሜይዴይ የድረሱልኝ ጥሪ ስርጭትን ይመለከታል። ይህ መልዕክት "Charlie" በተባለው ክስተት ውስጥ የነበረችው አነስተኛ ጀልባ ለአደጋ መጋለጧን የገለጸ ሲሆን፣ በአካባቢው ለሚገኙ ማናቸውም የውኃ ላይ መጓጓዣዎች ምላሽ እንዲሰጡ ትእዛዝ አስተላልፏል። የሜይዴይ የጥሪ መልዕክት በተላለፈበት ወቅት ለ"Charlie" ክስተት ቅርብ የነበረችው መርከብ በፈረንሳይ የባሕር ዳርቻ ጥበቃ አገልግሎት ላይ የነበረችው ፍላማንት (Flamant) የተሰኘችው የፈረንሳይ የጦር መርከብ ነበረች።

HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ለምርመራው በሰጠው ማስረጃ መሠረት፣ Flamant ጥሪው ከተላለፈበት ትክክለኛ የቦታ መገኛ ነጥብ በግምት 3 nautical miles (የባሕር ማይል) ወይም የ15 ደቂቃ ጉዞ ርቃ ትገኝ ነበር። በተቃራኒው፣ የድንበር ኃይል መርከብ የሆነችው Valiant በግምት 9 nautical miles (የባሕር ማይል) ወይም የ40 ደቂቃ ያህል ርቀት ላይ ነበረች። ይሁን እንጂ Flamant ለቀረበው የሜይዴይ የድረሱልኝ ጥሪ ምላሽ ሳትሰጥ ቀርታለች።

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፣ የመርከቧ ድርጊቶች እና ግድፈቶች በየፈረንሳይ ባለሥልጣናት በኩል ምርመራ እየተካሄደባቸው ይገኛል። ሆኖም ግን፣ የሜይዴይ ጥሪው በተላለፈበት ወቅት Flamant ለ"Charlie" ክስተት የነበራት ቅርበት እንዲሁም፣ በወቅቱ የአነስተኛዋ ጀልባ ደህና መሆኗን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ Flamant በቦታው ተገኝታ ቢሆን ኖሮ -- የብዙዎች -- ምናልባትም የሁሉም -- ሕይወት ይተርፍ ነበር።

ከፍለጋ እና ነፍስ አድን ጥረቱ ጋር የተያያዘው ተጨማሪ ነጥብ፣ በዚያች ሌሊት በHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ በኩል የታየውን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ይመለከታል። ሪፖርቱ ለዚህ ጉዳይ ጥልቅ ትኩረት ይሰጥአል። HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ በካናሉ በኩል

ባሕር ለማቋረጥ በአነስተኛ ጀልባዎች የሚደረጉ ጉዞዎችን በተመለከተ ትክክለኛ እና አስተማማኝ መረጃ በማግኘት ረገድ ከፍተኛ ችግሮች እንደሚገጥሙት የምቀበል ቢሆንም ተቋሙ ከኖቬምበር 2021 ዓ.ም በፊት ስለነበሩት ችግሮች ግንዛቤ ነበረው።

በዚያው ዓመት ኖቬምበር 23 ከነበረው የሌሊት የሥራ ፈረቃ ጀምሮ፣ HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ በDover Strait በኩል ባሕር ለማቋረጥ በአነስተኛ ጀልባዎች የሚደረጉ ጉዞዎችን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ በማጣቱ ምክንያት ሥራው ተስተጓጉሎ ነበር። በነበረው የአየር ሁኔታ ሳቢያ በዚያች ሌሊት የክትትል በረራ (surveillance flight) ለማድረግ አልተቻለም። በየፈረንሳይ ባለስልጣናት በኩል የቀረበው መረጃ አነስተኛ እና ዘግይቶ የደረሰ ሲሆን፣ በአካባቢው በነበሩ መርከቦች በኩልም ለቀረበው ሜዴይ ጥሪ አጥጋቢ ምላሽ አልተሰጠም።

ሆኖም በDover የሚገኘው የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ የየፍለጋ እና ነፍስ አድን ተልዕኮ አስተባባሪ ከሌሊቱ 1.48 ኤ.ኤም. ላይ ከ "Charlie" የተሰኘው ክስተት የመጀመሪያውን ጥሪ ሲቀበል፣ ሁኔታው ድንገተኛ አደጋ ሊሆን እንደሚችል በትክክል ተገንዝቦ ነበር።

ይህ ግምገማ በአስተባባሪው ቢደረግም፣ ከመደበኛ የአሠራር ሥርዓቶች ውጭ በሆነ መልኩ፣ HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ከሌሎች ደዋዮች ዝርዝር መረጃዎችን ለማሰባሰብ ያደረገው ሙከራ ውስን የነበረ ሲሆን፣ ከአነስተኛዋ ጀልባ በቀጥታ የተገኘው መረጃ እንደ ቁምነገር አልተወሰደም ነበር። HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ከጀልባዋ ጋር ግንኙነት በተደረገባቸው ወቅቶች ትክክለኛውን የጂኦሎኬሽን (geolocation) መረጃዎችን ለማግኘት የሚረዱ አጋጣሚዎችን ሳይጠቀምባቸው ቀርቷል።

በHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ መሪነት በValiant እና በሄሊኮፕተር R163 በተካሄዱት የፍለጋ ሥራዎች ወቅት፣ ተጨማሪ የማዳን ዕድሎች ባክነዋል። ጀልባዋ እየሰመጠች መሆኑን ወይም ሰዎች ባሕሩ ላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለአንዳቸውም የተሰጠ መረጃ አልነበረም። ሁለቱም ሙሉ የፍለጋ መመሪያዎች አልደረሷቸውም ነበር። በእርግጥም፣ HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ለ "Charlie"፣ ሥርዓቱን የጠበቀ የፍለጋ ዕቅድ አላዘጋጀም ነበር።

በዩናይትድ ኪንግደም የፍለጋ እና ነፍስ አድን፣ አነስተኛዋ ጀልባ ላይ የነበረ ማንንም ሰው ለማግኘት አልተቻለም። በሌሊቱ የነበረው የአየር ሁኔታ፣ አነስተኛዋ ጀልባ ላይ የነበሩት ሰዎች ለምን ሳይገኙ ቀሩ ለሚለው ጥያቄ ከፊል መልስ ብቻ ይሰጣል። በሪፖርቱ ውስጥ በዝርዝር እንደተገለጸው፣ በፍለጋ እና ነፍስ አድን ሥራው ላይ የታዩት እነዚህ ግድፈቶች፣ የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ የሥራ ድክመት ውጤቶች ናቸው። እነዚህ ስህተቶች የValiant ወይም የሄሊኮፕተር R163 ካፒቴን እና ሠራተኞች ኃላፊነት ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም። በዚያች ሌሊት የተከናወነው የፍለጋ እና ነፍስ አድን ኦፕሬሽን፣ አጠቃላይ ይዘት ባጭሩ ሲገለጽ ይህንን ይመስል ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ በኖቬምበር 24 ቀን 2021 በጠዋቱ ያለጊዜው የፍለጋ ሥራው እንዲያበቃ ተደርጓል። በሪፖርቱ ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ በDover የሚገኘው HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ በValiant የተገኘችውን ሁለተኛዋን አነስተኛ ጀልባ እንደ "Charlie" ክስተት በመቁጠር በስህተት ለይቷታል። "Charlie" ስለተሰኘው ክስተት ተይዞ በነበረው መረጃ እና በሁለተኛዋ አነስተኛ ጀልባ መካከል ግልጽ የሆነ ቅራኔ ቢኖርም ይህ ስህተት መፈጠር ችሏል። ለዚህ ውሳኔ ዋና ምክንያቶች፣ በጽሑፍ አልተመዘገበም እና በመረጃ አያያዝ ሂደት ላይ ሌሎች ግድፈቶች ነበሩ። በመረጃ አያያዝ ረገድ የታዩ ክፍተቶች፣

የቀን ፈረቃ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች "Charlie" የተሰኘው ክስተት በስኬት ተጠናቋል ብለው እንዲያምኑ ምክንያት የሆነ ሲሆን፣ በዚህም የተነሳ፣ Valiant ፍለጋውን ባጠናቀቀበት በ6:46 ኤ.ኤም እና በፈረንሳይ ባሕር ክልል አስከሬኖች መገኘታቸው ሪፖርት በተደረገበት በ12:57 ፒ.ኤም መካከል ባለው ወሳኝ ስድስት ሰዓት ውስጥ፣ በውቃው ላይ በሕይወት ተርፈው ለነበሩት ሰዎች በHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ በኩል ምንም ዓይነት የነፍስ አድን ሙከራ ሳይደረግ ቀርቷል።

ይህ ባይሆን ኖሮ፣ HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ስሌት መሠረት በሕይወት ለመትረፍ በ የሚያስችለው የመጨረሻው የጊዜ ገደብ እስኪጠናቀቅ ድረስ ፍለጋው ይቀጥል የነበረበ ሲሆን፤ ፍለጋው ቢያንስ እስከ ኖቬምበር 24 ቀን 2021 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ይዘልቅ ነበር። የእይታ ሁኔታም ሆነ የሌሊቱ ጨለማ ፍለጋውን ሊያስተጓጉሉ አይችሉም ነበር። ሄሊኮፐተር R163 በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ ከአየር ላይ ሆኖ አስከሬኖቹን በቀላሉ ማግኘት ችሏል። በሕይወት ያሉ ሰዎችን የማዳን ሥራ በዚያኑ ዕለት የቀኑን ብርሃን በመጠቀም በበቂ ሁኔታ ተከናውኖ ቢሆን ኖሮ፣ የ ብዙዎችን ሕይወት ማትረፍ ይቻል ነበር።

የሪፖርቱ ምርመራ በግልጽ እንደሚያሳየው፣ በHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የታዩት ግድፈቶች በተፈጥሮአቸው መሠረታዊ የሆነ የተቋማዊ አሠራር ችግሮች ነበሩ። በተለይም፣ እነዚህ ችግሮች ከሚከተሉት ምክንያቶች የሚመነጩ ናቸው፡- (i) በDover የአነስተኛ ጀልባዎች ፍለጋና ነፍስ አድን ሥራ ላይ የተሰማሩ የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ሠራተኞች፤ በሰው ኃይል እጥረትና በሌሎች ጉድለቶች ምክንያት ሊቋቋሙት የማይችሉት ከፍተኛ ጫና መኖር፤ (ii) በእነዚያ ሠራተኞች ላይ የሚደረግ ውጤታማ

የቅርብ ክትትልና አመራር (supervision) አለመኖር፤ (iii) ለሠራተኞቹ ድጋፍ እንዲሰጥ የተቀረጸው የርቀት አሠራር (remote working model) የነበሩበት ክፍተቶች፤ እና (iv) አራተኛ፣ ከአነስተኛ ጀልባዎች የሚደውሉ ሰዎች ያሉበትን አስከፊ ሁኔታ አጋንነው ያቀርባሉ የሚለው በHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ዘንድ የነበረው አመለካከት።

በመጨረሻ ወደ ሪፖርቱ ምክረ ሐሳቦች እሸጋገራለሁ። ከ ኖቬምበር 2021 ዓ.ም ጀምሮ HM የባህር ዳርቻ ጠባቂ ባለው የሰው ኃይል እና የቁሳቁስ አቅርቦት ረገድ ብዙ ማሻሻያዎች ማድረጉን አስቀድሜ መጥቀስ እፈልጋለሁ። በተጨማሪም በሪፖርቱ የመጨረሻ ክፍል ላይ እንደገለጽኩት፣ ስለ አደጋው ቀደም ብለው የቀረቡ የሦስት ሪፖርቶችን ምክረ ሐሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ ጥረቶች የተደረገ ሲሆን፣ ይህም ቀደም ብዬ የጠቀስኩትን የMAIB ሪፖርት፣ በጁላይ 2023 ዓ.ም የተዘጋጀውን የUS የባህር ዳርቻ ጠባቂ የባለሙያዎች ግምገማ እና በሜይ 2024 ዓ.ም ለመጨረሻ ውሳኔ ያልቀረበ የHM Coastguard የውስጥ ግምገማን ያጠቃልላል።

ሦስቱም ሪፖርቶች ምክረ ሐሳቦችን ያካተቱ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ ተቀባይነት አግኝተው ተግባራዊ ሆነዋል። ሆኖም ግን የUS የባህር ዳርቻ ጠባቂ ያቀረባቸው በርካታ ነጥቦችን ጨምሮ፣ ሌሎች ምክረ ሐሳቦች ተቀባይነት ሳያገኙ ቀርተዋል። በተጨማሪም የHM የባህር ዳርቻ ጠባቂ የውስጥ ግምገማ፣ የምርመራ ሂደቱ ያጋለጣቸውን ዋና ግድፈቶች አላካተተም።

በሪፖርቱ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይም የራሴን ምክረ ሐሳቦች በዝርዝር አስፍሬያለሁ። እነዚህ ምክረ ሐሳቦች፣ አደጋው ከተከሰተባቸው ዓመታት ወዲህ እስካሁን የተመዘገቡ መሻሻሎችን ሙሉ በሙሉ ከግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው። እነዚህ ምክረ ሐሳቦች

በአራት ዋና ዋና ምድቦች ተከፍለዋል። እነዚህም፣ የምርመራ ቡድኑ ከተሰጠው የሥራ መመሪያ በመነሳት፣ ወደፊት ተመሳሳይ ክስተት የመከሰት ዕድሉን ለመቀነስ ታስበው የቀረቡ ናቸው። ምድቦቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

(1) ባሕር ለማቋረጥ በአነስተኛ ጀልባዎች የሚደረጉ ጉዞዎችን በሚመለከት የቀረቡ የፍለጋ እና የማዳን ምክረ ሐሳቦች

(2) በአጠቃላይ በበርካታ ሰዎች ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን በሚመለከት የቀረቡ የፍለጋ እና የማዳን ምክረ ሐሳቦች

(3) በባሕር ላይ ፍለጋ እና ማዳን ተግባራት ውስጥ ያሉ መዋቅራዊ እና ሕጋዊ ችግሮችን ለመፍታት የቀረቡ ምክረ ሐሳቦች፤ እና

(4) ቀደም ሲል እንደገለጽኩት፣ የMAIB የምርመራ ሪፖርት ምክረ ሐሳቦች አፈጻጸምን የሚመለከቱ መረጃዎች ለሕዝብ ግልጽ ሆነው እንዲቀርቡ የሚያሳስብ አጠቃላይ ምክረ ሐሳብ።

አሁን የምክረ ሐሳቦቹን ሙሉ ዝርዝር በሪፖርቱ ምዕራፍ 17 ውስጥ ማግኘት ይቻላል። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፣ ከኖቬምበር 23 እስከ 24 ቀን 2021 የደረሰው ዓይነት ከፍተኛ የሰዎች ሕይወት የሚቀጥፍ አደጋ እንዳይደገም ማድረግ የዚህ ምርመራ አንዱ ዋና ግብ ነው። የ አቀረብኳቸው ምክረ ሐሳቦች የተቀረጹት ይህንኑ ግብ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ ነው። ሆኖም ግን ይህን የሚያደርጉት ከተተገበሩ ብቻ ነው። የምርመራ ቡድኑ ሪፖርቱ ከታተመ በኋላ የምክረ ሐሳቦቹን አፈጻጸም ለመከታተል የሚያስችለው አሠራር ስለሌለው፣ መንግሥት በምክረ ሐሳቦቹ አፈጻጸም ላይ የሚታዩ መሻሻሎችን ለሕዝብ ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነትን መውሰዱ እጅግ አስፈላጊ ነው።

በሪፖርቱ ላይ እንደገለጽኩት፣ ይህንን ሂደት በማንኛውም ተገቢ በሆነ መንገድ ለመደገፍ ዝግጁ መሆኔን አረጋግጣለሁ። ስለሚታዩ መሻሻሎች ሪፖርት ማቅረብ እና ገለልተኛ ክትትል ማድረግ፣ በምርመራው ሂደት ላይ የሕዝብን አመኔታ እና መተማመንን ለማጠናከር የሚረዱ መንገዶች ናቸው።

በመጨረሻም፣ በሪፖርቱ መግቢያ ላይ እንደገለጽኩት፣ ባሕር ለማቋረጥ በአነስተኛ ጀልባዎች የሚደረጉ ጉዞዎች ሊቆሙ ይገባል። ከሌሎች ምክንያቶች ባሻገር፣ ተጨማሪ የሰው ሕይወት እንዳይጠፋ መከላከል እጅግ አስፈላጊ ነው። ለባሕር ጉዞ ብቁ ባልሆነ እና ከሚችለው በላይ ሰው በጫነ አነስተኛ ጀልባን ተሳፍሮ፣ በዓለም ላይ ካሉ እጅግ በጣም ሥራ ከበዛባቸው የንግድ መርከብ መተላለፊያ መንገዶች አንዱን ለማቋረጥ መሞከር በራሱ አደገኛ የሆነ ተግባር ነው።

በጣም እናመሰግናለን!